# ቀስተ ደመና ሬድዮ

## ትችት (06/12/02)

## የርዳታው እህል እውን መርዝ ነው??

በአንድ አካባቢ ርሃብ በተከሰተ ቁጥር በእርዳታም ሆነ በልማት መስክ በተሰማሩ ድርጅቶችም ሆነ ያገባናል በሚሉ የሲቪክም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች አካባቢ የሚነሱ አይቀሬ ክርክሮች አሉ። የርሃቡ መሰረታዊ ምክንያት ምንድን ነው? ርሃቡ ተፈጥሮዋዊ ነው ወይስ ሰው ሰራሽ? እንዲህ ያለው አደጋ ተመልሶ እንዳይከሰት ምን እርምጃዎች መውሰድ ያስፈልጋል? እርዳታ በገፍ ቢገባ ያለውን መንግስት ያጠናክራል ወይስ ያዳክማል? እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ክርክሮች የቆዩና አሁንም ያሉ ክርክሮች ናቸው። በነዚህ ላይ ደግሞ ከጥቂት አመታት ወዲህ ሌላ ክርክር ተጀምሮ ነበር። ለተራቡ አገሮች የሚሰጠው ርዳታ በምን መልክ መሆን አለበት? የሚል ጥያቄ ይነሳ ነበር። የዚህ ክርክር ይዘት ምንድን ነው?

በአንድ በኩል አንድ አገር ድርቅ ገባ ሲባል ይህ ድርቅ በተወሰነ አካባቢ እንጂ በመላው በሃገሪቱ ላይከሰት ይችላል። በዚህ በተባለው አገር አንዳንድ አካባቢዎች ምርት ባይሳካም በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ ትርፍ የሚመረትበት ሁኔታ አለ። ስለዚህ ለዚች አገር ርሃብተኞች የሚሰጠው ርዳታ በተቻለ መጠን በገንዘብ መልክ ሆኖ በዚህ ገንዘብ እህል ከዛው አገር የውስጥ ገበያ መገዛት አለበት። ይህ ከሆነ የዚያ አገር ትርፍ አምራች ገበሬዎች ይጠቀማሉ። በእህል መልክ ከውጭ ከገባ ግን እነዚህ ገበሬዎች ለኪሳራ ይዳረጋሉ። ለማምረት ምንም ማበረታቻ አያገኙም። ስለዚህ የነዚህ አገሮች የእርሻ ዘርፍ እድገት ይሰናከላል። ርሃብም ይህንን አገር ደግሞ ደጋግሞ የሚያጠቃበት ሁኔታ ይፈጠራል።

በሌላ በኩል ደግሞ እህሉም የኛ ነው ገንዘቡም የኛ ነው ስለዚህ በኛ ገንዘብ ከኛው ገበሬዎች ገዝተን ርዳታ ማቅረብ አለብን እንጂ የኛ እያሉ ከሌሎች ገበሬዎች አንገዛም የሚሉ አሉ። በዚህም የተነሳ አንድ አገር ርሃብ ገባ ሲባል ለነዚህ ወገኖች የሚታያቸው በዚያ አገር ከተራበው ህዝብ ቁጥር የሚመጣጠን ገበያ መከፈቱ ነው ማለት ነው።

በሁለቱ እይታዎችና አሰራሮች መሃከል የቆየው ክርክር ዛሬም እልባት አላገኘም። በአጠቃላይ ማለት የሚቻለው ግን እንደ አውሮፓ ህብረት ያሉ ዋና ዋና ለጋሾች በመጀመሪያው አቋዋም ተሰማርተው በተቻለ መጠን እርዳታ በገንዘብ መልክ ሲሰጡ በርሃብ ርዳታ በአለም ከፍተኛ ድርሻ ያላት አሜሪካ ደግሞ ይህንን እርዳታ በእህል መልክ የማቅረብ አወዛጋቢ ፖሊሲዋን ቀጥላለች።

ይህ ልዩነት በዚህ እንዳለ አሁን ደግሞ ብዙ ስሜትና ምሬት፤ መወነጃጀልና መመፃደቀ የተደበላለቀበት ሌላ ክርክር ከጥቂት ወራት ወዲህ እየጦፈ መጥቷል። ለእርዳታ የሚቀርበው ምን አይነት እህል ነው? የወያኔ ባለስልጣናት ይህ ክርክር እየተጡዋጡዋፈ በመካሄድ ላይ እንዳለ ያውቃሉ። ግን በይፋ ምንም ያሉት ነገር የለም። የህዝብ ጉዳይ ያገባናል ብለው በተቃዋሚነት የተደራጁ ሃይሎችም በነገሩ አልገቡበትም። የዚህን ምክንያት ሌላ ጊዜ እንመለስበታለን። ለጊዜው ግን ስለውዝግቡ ይዘት ትንሽ እናብራራ።

እዚህ ትርምስ ውስጥ አሁንም መሃከላዊ ቦታ የያዘው የአሜሪካኖች ፖሊሲ ነው። በእርዳታ የሚያቀርቡት እህል ' ጄነቲካሊ ሞዲፋይድ ፉድ" የሚባለው ነው። ማለትም ዘሩ የተቀየረ ምግብ። ግዙፍና ከአሜሪካን የእርሻ ሚኒስቴርም ሆነ ዩኤስ እይድ ከተባለው የአሜሪካ የርዳታ ድርጅት ጋር ተቆራኝተው የሚሰሩ ታላላቅ የእርሻ ምርምር፤ የምግብና የዘር ኩባንያዎች ገበያቸውን በመላው አለም ለማስፈን ዘሮችን አዳቅለው፤ አንዳንድ ኬሚካል ጨምረውባቸውና ተፈጥሮዋዊ ይዘታቸውን ቀይረው ያመርታሉ። በዚህ መልክ ተሻሻሉ ተብለው የሚዘሩት ዘሮች ድርቅን በተሻለ የመቋዋቋዋም ጠባይ አላቸው፤ በሰብል ተባይ እንዳይጠቁ ከወዲሁ ተከትበዋል፤ ከነሱ የሚገኘው ምርት ተፈጥሮዋዊ ከሆነ ዘር ከሚገኘው እጥፍ ድርብ ነው ወዘተ የሚሉ መከራከሪያዎች ይቀርባሉ።

በዚህ መልክ የተመረተ ሰብል እጅግ አወዛጋቢ እየሆነ መጥቷል። ይህ አይነት ሰብል በአውሮፓ ገበያ እንዳይቀርብ ከብዙ አመታት ወዲህ የታገደ ነው። በያዝነው ሳምንት የወጣ አንድ ዜና በዚህ እገዳ ምክንያት የአሜሪካን መንግስት በአለም የንግድ ድርጅት በአውሮፓ ህብረት ላይ ክስ ለመመስረት ማሰቡ ተዘግቧል። በርሃብ አለንጋ በምትሰቃየው አፍሪካም ይህ እህል በርዳታ መልክ እንዳይገባ ብዙ ተቃውሞ እየገጠመው ነው።

እንደሚታወቀው ዘንድሮ የደቡባዊ አፍሪካ አገሮችንም ርሃብ እያጠቃ ነው። ይህንን ለመቋቋቋም እንዲረዳ የ አሜሪካን መንግስት በመቶ ሺ ቶን የሚለካ ከተቀየረ ዘር የበቀለ እህል ለርሃብተኛው አስቸኩዋይ ርዳታ አቀርባለሁ አለ ። ይህ ውሳኔ በአካባቢው መንግስታት መሪዎች፤ በአለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሌላው ቀርቶ በተባበሩት መንግስታት አንዳንድ ባለስልጣኖች አካባቢ ከፍተኛ ተቃውሞ አጋጠመው።

የዚምባብዌው ፕሬዜዳንት ሮበርት ሙጋቤ ይህንን ርዳታ ለምን እንደማይቀበሉ ለማብራራት ባደረጉት ንግግር “ ይህንን ርሃብ የምንዋጋው አይናችንን የኢኮኖሚያችን የጀርባ አጥንት በሆነው የሃገራችን የእርሻ ዘርፍ የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ ተክለን ነው። በጭንቀትና በተስፋ መቁረጥ ላይ በተመሰረቱ አጉዋጉል ውሳኔዎች ይህንን ዘርፍ አደጋ ላይ እ ንዳንጥል መጠንቀቅ ይናርብናል።“ ሲሉ ተደምጠዋል።

ዛምብያ በበኩሉዋ ልቀበል አልቀበል የሚለውን ጥያቄ ከመመለሱዋ በፊት በደቡብ አፍሪካ፤ በአውሮፓና በአሜ ሪካ ተዘዋውሮ ስለዚህ ምግብ ጥናት የሚያካሂድ የሳይንቲስቶች ቡድን ላከች። ቡድኑ ሲመለስ ባቀረበው ሪፖርት በመ መርኮዝ የሃገሪቱ ፕሬዜዳንት ሌቪ ሙዋናዋስቦ ባደረጉት ንግግር ይህንን እህል “ መርዝ ” ብለው ከጠሩት በኃላ ” የዛ ምብያ ህዝብ ይህንን የተመረዘ እህል ከሚበላ መሞትን ይመርጣል” እንዳሉ ተዘግቧል።

ማላዊ በበኩሏ ለመጠባበቂያ የተከማቸውን እህል ከጥቂት ወራት በፊት በአለም የገንዘብ ድርጅት ወይም አይ ኤምኤፍ ግፊት ብድር ለመክፈል ተብሎ ሸጣ የተራቆተች አገር ነች። አሁን ባለው ችግር ትንሻ ካቅማማች በኃላ እቀ በላለሁ አለች። በመሃል የሞዛምቢክ መንግስት ወደ ማላዊ ለመሄድ በኔ ምድር ላይ የሚያልፈው እህል  ከባቡር እየተን ጠባጠበ መሬቴን እንዳይበክል በሚገባ በፕላስቲክ ታሽጎ መሆን አለበት። አለበለዚያ ይህ እህል በግዛቴ ላይ አያልፍም አለ።

በአለም አቀፍ ደረጃ እንደ ኦክስፋምና አክሽን ኤይድ የመሳሰሉት ታላላቅ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይህ ንን አይነት እርዳታ በመቃወም ከፍተኛ አለም አቀፍ ዘመቻ ይዘዋል። የአሜሪካኑ ዩኤስ ኤይድ የርዳታ ድርጅት ሃላፊ የሆኑት ባለስልጣን እየተጧጧፈ ያለውን ክርክርና ይህንን እህል አንቀበልም የሚሉትን ወገኖች ለማጥላላት ነገሩን አቅል ለው ” በበለፀጉት ሃገሮች ያሉ የተመቻቸውና ርሃብ ምን እንደሆነ የማያውቁ ሰዎች በርሃብተኛው ቦታ ሆነው ሊወስኑ አ ይችሉም። ሌላ ምርጫ በሌለበት ሁኔታ ይህንን ምግብ መቃወም ማለት ህዝብ በርሃብ ቢያልቅ ግድየለንም የሚል ሃላፊ ነት የማይሰማው አቋዋም ነው።” በሚል መንፈስ መግለጫ ሰጥተዋል። ዣን ዚግለር የተባሉት የተባበሩት መንግስታት የ ምግብ ሴኩሪቲ ጉዳይ ተከታታይ ወይም ሪፖርተር የሆኑት የስዊስ ተወላጅ ደግሞ ለዚህ መልስ ሲሰጡ “ ከተለወጠ ዘር የተመረተን እህል መቃወም ርሃብ በአለም እንዲቀጥል ማገዝ ነው የሚለው አቋዋም ተቀባይነት የለውም። ውሸት ነው ። ዛሬ በአለም ላይ አሁን ካለው ህዝብ እጥፉን ሊመግብ የሚችል ጤናማና ተፈጥሮዋዊ የሆነ እህል አለ።” ሲሉ የአሜ ሪካኑን መንግስት ባለስልጣን አቋዋም በማጥላላት ክርክሩ ውስጥ ገብተዋል።

ይህንን ካልበላችሁ ምርጫው መራብ ነው የሚለው አቀራረብ ልክ አይደለም። ብዙ ታዛቢዎች ከዚህ አንፃር የ ሚያቀርቡዋቸው አሃዞች በጣም ግልፅ ናቸው። የአለም የምግብ ፕሮግራም የተባለው የተመድ ተቋዋም እንደሚለው ከሆ ነ ለደቡባዊ አፍሪካ አምስት አገሮች በመጭዎቹ ወራት ሁለት ሚልዮን ቶን እህል ርዳታ ሲያስፈልግ  ሌላው ቀርቶ በ ኬንያ፤ ታንዛንያና ዩጋንዳ ብቻ አንድ ሚልዮን ስድስት መቶ ሺ ቶን ትርፍ ተፈጥሮዋዊ እህል አለ። እንደቻይና፤ ህንድ ወዘተ በመሳሰሉት አገሮች ደግሞ በደርዘን ሚልዮን የሚቆጠር ተፈጥሮዋዊ እህል በጣም በርካሽ ይገኛል። ወይ ይህንን ብሉ ወይ እለቁ የሞለው ክርክር አጉል ክርክር ነው።

እንግዲህ ጥያቄው ግልፅ ነው። ይህንን ሁሉ ማእበል እያስነሳ ያለው ከተለወጠ ዘር የተመረተው እህል ወይም ጄነቲካሊ ሞዲፋይድ ፉድ የሚባለው የዛምብያው ፕሬዜዳንት እንዳቀረቡት እውን መርዝ ነው?? አይመስለንም። ይህ በ ሳይንሳዊ ምርመራ ገና የተረጋገጠ ነገር አይደለም። እንደዛምብያው ፕሬዜዳንት ዛሬ ለሃገራችን ርሃብተኛ ሌላ ካልተገኘ ይህንን ከመብላት መሞት ይሻልሃል አንልም። አንዳንድ ሰማቸውን ለጊዜው የማንጠራው የኢትዮጵያውያን ዌብ ሳይት ላይ እንደታዘብነውም ” ከዚህ ምግብ ይልቅ የኢትዮጵያ ህዝብ ክብሩን ጠብቆ መሞት ይሻለዋል።” የሚልም አጉዋጉ ል አቋዋ አናንፀባርቅም። ምርጫ ከሌለና ለጊዜው ነፍስ ለማቆየት የግድ ከሆነ ተቀብለን እንበላለን።

መርዘኛነቱ አልተረጋገጠም። የአውሮፓ ህብረት ይህ ምግብ በአውሮፓ ገበያ እንዳይቀርብ ሲከለክል ‘ ምግቡ
መርዘኛነቱ ተረጋግጡዋል” በሚል ክርክር አይደለም። ጤናማ ለመሆኑ ማረጋገጫ የለም በማለት “ ፕሬኮሺናሪ ፕሪንሲ
ፕል” ወይም “ የጥንቃቄ መርህ” የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ በማስቀደም ነው። እንዲያውም በኛ አስተያየት ከባዱና አስጨ
ናቂው ጥያቄ የዚህ እህል በአጭር ጊዜ መርዘኛ መሆን ወይም አለመሆን ጥያቄ አይደለም። ክርክሩ እዚህ ላይ እንዲያ
ተኩር ማድረግ ለነዚህ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ስፊ የማደናገሪያ በር መክፈት ነው። ሌላ ይበልጥ አሳሳቢ ችግርም አ
ለና። ሰሞኑን በዚህ ላይ የሚተቹ ሁሉ ነገሩን ከረጅም ጊዜ መዘዙ አንፃር በማየት ይህንን የተለወጠ ዘር የማስፋፋት ዘ
መቻ “ በድሃ አገሮች ገበሬዎች ላይ የተከፈተ የባዮቴክኖሎጂ ጦርነት” ብለው እስከ መጥራት ሄደዋል። ለምን?

በአለም አቀፍ ደረጃ በዚህ በምግብ ምርምር፤ በዘር ምርትና ንግድ መስክ የተሰማሩት እንደ ሞንሳንቶ፤ ኖቫ ት
ሪስ፤ ሃይ ብሪድ ኢንተርናሽናል አይነቶች ግዙፍና ድንበር ዘለል የሆኑ ኩባንያዎች አካሄድ በነዚህ በተለወጡ ዘሮች አ
ማካኝነት በማራመድ ላይ ያሉት የአለምን የግብርና የስራ መስክ ብሎም አንድ ቢልየን ተኩል የሚገመቱ ድሃ ገበሬዎች
ን ከመደፋቸው ለመክተት የሚያስችል ስትራቴጂ ነው። ውስብስቡን ነገር በቀላሉ ለማስቀመጥ በነዚህ ግዙፍ ኩባንያዎ
ች የሚፈጠሩት ዘሮች አንዳንዴ “ተርሚናቶር“ በሚል ስም ይታወቃሉ። ፈፃሚ ማለት ነው። ተቀይሩዋል፤ የሰብል ተባ
ይን ለመቋዋቋዋም እንዲችል ተከትቡዋል፤ ከአንዲት ጥሬ የሚገኘው ምርት እጥፍ ድርብ እንዲሆን ተመቻችቱዋል የ
ሚባልለት አዲስ ዘር በእርግጥ ለድሃ ገበሬዎች አደገኛ ነው። አፈሩን ይበክላል። ሌላም ዘግናኝ መዘዝ አለው። ተመር
ቶ ይበላል እንጂ ከዚህ ዘር የበቀለ ጥሬ ተመልሶ ቢዘራ አይበቅልም። ስለዚህ እዚህ ወጥመድ ውስጥ የገቡ ገበሬዎች የ
ሚኖራቸው ምርጫ በየአመቱ ለመዝራት ከፈለጉ በየአመቱ መልሰው መላልሰው ዘር ከነዚህ ኩባንያዎች ለመግዛት ይገ
ደዳሉ ማለት ነው።

በዚህ ጉዳይ ያለው መሰረታዊ ክርክር ዛሬ የተራበው ህዝብ ምርጫ ካጣ ይህንን እህል ይብላ አይብላ የሚለው
አይደለም የምንለውም ለዚህ ነው። መጋለጥ ያለበት በዚህ መልክ የአለምን ገበሬዎች ወጥመድ ውስጥ ሊጥል የሚችለ
ው አሰራር ነው። ለጊዜው የደቡባዊ አፍሪካ አገሮች የነፍስ አድን ጥረቱን ሳያደናቅፉ የረጅም ጊዜውን አደጋ ለመከላከ
ል እንድችሉ አንድ መፍትሄ አግኝተዋል። ይኸውም በእርዳታ የሚገባው እህል ችግረኛ ገበሬ እጅ ገብቶ እንዳይዘራ በ
ዱቄት መልክ ብቻ እንዲገባ መወሰኑ ነው።

በዚህ አሳሳቢ ጉዳይ የወያኔዎች ፖሊሲ ምን እንደሆነ በግልፅ የሚታወቅ ነገር የለም። ባለፉት አመታት ያሳዩት
አሰራር ሲታይ ግን ሁኔታው እስከዚህም የሚያስተማምን አይደለም። ከነዚህ በአለም ገበሬዎች ላይ ከሚያሴሩት ግዙፍ
ድበር ዘለል ኩባንያዎች ቀንደኛው ሃይ ብሪድ ኢንተርናሽናል የተባለው ኩባንያ ነው። ኩባንያው ላለፉት ስምንት አ
መታት በወያኔ ሞኖፖሊነት ከሚንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ የዘር ኢንተርፕራይዝ ከተባለው ተቋዋም ጋር እጅና ጉዋንት ሆ
ኖ ሲሰራ ቆይቷል። የዛሬ ሁለት አመት አንድ ካናዳዊ የዩኒቨርሲቲ ምሁር “ በኢትዮጵያ የርሃብ ዘር እየተዘራ ነው” (ወ
ይም ሶዊንግ ዘ ሲድስ ኦፍ ፋሚን ኢን ኢትዮፕያ) በሚለው ጥናታቸው ላይ በዚህ ኩባንያ ግፊትና ድጋፍ የደርግ መንግ
ስት ‘ሲድስ ኦፍ ሰርቫይቫል“ (ወይም ዘር ለማትረፍ) ከተባለ አለም አቀፍ የልማት ድርጅት ጋር በመተባበር በየገጠሩ
አቁዋቁሙዋቸው የነበሩትን የዘር ባንኮች ወያኔ እንዴት እንዳፈረሳቸው ተዘግቡዋል። ይህንን ስናይ ቀደም ብሎ በተረጋ
ጋ ሁኔታ እያለ እንዲህ አይነቱን ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ገበሬ አቋዋም የያዘ መንግስት አሁን በተነሳው ክርክር ህዝባዊ የ
ሆነ አቋዋም ይዞ አለመከራከሩ ምንም አይደንቀንም። የሚደንቀው ነገር በዚህ ቁልፍ ጥያቄ ላይ የፖለቲካ ሃይሎችም
ሆኑ ሲቪኩ ማህበረሰብ በማሳየት ላይ ያለው ዝምታ ነው።